# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፡፡

# Ethiopia: The Kingdom of God Services

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥ ኢትዮጵያውያንም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳት፥ የ"ኢትዮጵያ" እና "የኢትዮጵያውያን" የኾነውንም ኹሉ ለመጠበቅና ለማሳወቅ፡፡
To reveal the truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God; and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.

---

ነሓሴ ፳፬ ቀን፥ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

ይድረስ፡-

ለጀርመን ነፋስ ድምፅ፥
የኢትዮጵያኛው አገልግሎት ሹምና የሥራ ባልደረቦችዎ፤
ቦን ከተማ፤ ጀርመን፡፡

ኢትዮጵያዊ ሰላምታዬን፡ በእግዚአብሔር ስም አቀርባለሁ፡፡

የነፋስ ድምፃችሁን ዝግጅት ለማዳመጥ፡ ጊዜ አግኝቼ በተከታተልሁት ቍጥር፡ በሙያችሁ አቀራረብ፥ ይልቁንም፡ በቋንቋችን የቃላት አመራረጥ ረገድ የምታሳዩትን ጥንቃቄና ቆራጥነት እያስተዋልሁ እደሰታለሁ፤ ከዚህ የተነሣ፡ አገልግሎታችሁ፡ ለሌሎች፡ በአርአያነቱ ሊጠቅም እንደቻለና እንደሚችል፡ ያለኝ ግምት ትክክል ስለመኾኑ አልጠራጠርም፤ በዚሁ መልካም ይዘታችሁና አካኺዳችሁ ትጠናከሩበት ዘንድ፡ የበኩሌን የማበረታቻ አስተዋጽዖ፡ በዚህ አጋጣሚ፡ ይኸው አበረክታችኋለሁ፡፡

ይህን ደብዳቤ ለመጻፍ፡ ምክንያት የኾነኝ ቍም ነገር፡ በጋዛ፡ የእሥራኤል ዜጎች የኾኑት አይሁድ፡ በሠፈራ የያዙትን መንደር፡ በመንግሥታቸው ወታደሮች እየተገደዱ፡ ለባለመብቶቹ፡ ለፍልስጥኤማውያን የመልቀቃቸውን ዜና መነሻ በማድረግ፡ ሰሞኑን፡ በአቶ ነጋሽ መሓመድ አቅራቢነት የተላለፈው ሓተታ ነው፡፡

ይኸው ሓተታ፡ የአይሁድንና የፍልስጥኤማውያንን ታሪክ፡ በሶምሶንና በደሊላ ዘመን ጀምሮ፡ ዛሬ ሕያዋን ኾነው፡ በሕይወተ ሥጋ በሚኖሩት፡ በይሁዲው ሻሮንና በፍልስጥኤማዊው ሳዲቅ ይጨርሳል፤ በታሪኩ መጀመሪያና መጨረሻ መካከል ካሉት ተሳታፊዎች ውስጥ፡ የእስልምና መሥራቹ የመሓመድ አያትና በእስላማዊው የቱርክ አገዛዝ ጊዜ የነበረ፡ አንድ የእስልምና ፈላስፋ ሳይቀር ሲወሱ፡ ጥንት፡ በጋዛ፡ እስከባለርስትነት የደረሰ አግባብነት ያላቸው፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ብቻ፡ በምንም መልክ ሳይዘከሩ መታለፋቸውን በትዝብት ተገነዘብሁ፡፡ ይህ፡ ለምን እንደኾነ፡ በራሴ፡ ለማወቅ ሞከርሁ፤ "ማኅደረ ዜና" በሚለው በተደጋጋሚ ዝግጅታችሁ፡ እኒሁ፡ የተረሱ ጥቂዎች፡ ምናልባት፡ "ይጠቀሱ ይኾናል!" ብዬም ጠበቅሁ፤ ነገር ግን፡ እስከዚህ ጊዜ ድረስ፡ ስለእነርሱ፡ አንዳችም ነገር ያለመነሣቱን ሳረጋግጥ፡ እንዲህ ሊኾን የቻለበትን ምክንያት ለማወቅ ያህል፡ ይህን ደብዳቤ እጽፍላችሁ ዘንድ ተገደድሁ፡፡

የኢየሩሳሌም ቈርቋሪና ንጉሥ ስለኾነው፡ ስለኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ፡ የዓለሙ ታላላቅ ሃይማኖቶች በተቀበሉት፡ በቅዱሱ መጽሓፍ የተነገረውን፥ ተጽፎም የሚነበበውን፡ ለጊዜው ሳቆየውና፡ ኢየሩሳሌምንና ጋዛን በሚመለከት፡ ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያውያን፡ ከተመዘገቡት ውስጥ፡ ከየክፍሉ፡ አንድ አንዱን ብቻ፡ እስኪ ልጥቀሳቸው!

…፪

---

መልእ. ሣ. ቁ. ፰፻፲፪፤ ስልክ ቁ. ፲፮-፲፰-፹፭፤ ፳--፹፭፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡
P. O. Box 812, Tel. Nos. 16-18-85; 20-00-85, Addis Abeba, Ethiopia.
P.O.Box 43262, Washington, DC 20010-9262 U.S.A.
Tel. (301) 587-8074 ~ Fax: 301-587-1971 ~ E-mail: ekogyesus@aol.com
Website: www.ethkogserv.org

ከብሉዩ ኪዳን፡- *“የእግዚአብሔር ከተማ [ኢየሩሳሌም] ሆይ! እርሱ [እግዚአብሔር] ስላንቺ ያደረገው ነገር፡ ዕፁብ ድንቅ ነው፤ ፍልስጥኤምና ጢሮስ፥ <u>የኢትዮጵያም ሕዝብ፡ በዚያ ተወለዱ!</u>”* የሚለው ሲኾን፡ ከአዲሱ ኪዳን ደግሞ፡- *“የእግዚአብሔርም መልአክ፡ ፊልጶስን፡ 'ተነሥተህ፡ በደቡብ በኩል፡ ከኢየሩሳሌም፡ ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው፡ ምድረ በዳ ወደኾነው መንገድ ኺድ!' አለው፡፡ ተነሥቶም ኼደ፡፡ እነሆም፡ 'ሕንደኬ' የተባለች፡ የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ፡ በገንዘቧም ኹሉ የሠለጠነ፡ አንድ የኢትዮጵያ ሰው፡ ሊሰግድ፡ ወደኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር፤ ሲመለስም፡ በሠረገላ ተቀምጦ፡ የነቢዩን፡ የኢሳይያስን መጽሓፍ ያነብብ ነበር፡፡”* የሚለው ነው፡፡ እነዚህ ጥቅሶች፡ ስለተነሣንበት ርእሰ ጉዳይ፡ ምንን ያመለክታሉ? (*መዝ.* ፹፮ [፹፯]፥ ፬፡፡ የሓዋ. ፰፥ ፳፮-፳፯፡፡)

የአዲስ ኪዳኑ ኢትዮጵያዊ የመንግሥት ባለሥልጣን፡ በሠረገላ፡ ወደኢየሩሳሌም ኼዶ ሊሰግድ የተነሣው፡ ከየት፥ ሰግዶ፡ በዚያው መልክ የተመለሰውስ፡ ወደየት ኖርዋል? ከጋዛና ወደጋዛ መኾኑ ግልጽ ነው፡፡ እንደእርሱ ኹሉ፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት፡ በ፩ሺ ዓመት ግድም፡ የተፈጸመውን ተመሳሳይ ድርጊት፡ ሕያው ከኾነው፡ ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን የዜና መዋዕል ማኅደር አውጥተን ልናመሳክረው ይቻለናል፤ ይኸውም፡ የእሥራኤል ንጉሥ የነበረውን፡ ሰሎሞንን፡ ስለእውነተኛ ማንነቱና ሃይማኖቱ፥ በኢየሩሳሌም፡ የሚያሳንፀውም ቤተ መቅደስ፡ በእርግጥ ለእግዚአብሔር ስለመኾኑ ለማረጋገጥ፡ ራሷ፡ በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ፡ ፈጣሪ፡ በጥበቡ ያዘጋጀውን ዕቅድ ተከትላ፡ ከኢትዮጵያ ወደኢየሩሳሌም የተጓዘችው፥ ጓዟንም በጋዛ ያሣረፈችው፡ የኢትዮጵያዊቷ ስመ ጥር ንግሥት፡ የማክዳ ዝክረ ነገር ነው፡፡ “ጋዛ” የሚለው ስም፡ ከምን እንደተገኘ፡ ከዚሁ ዝክረ ነገርና በግእዝ፡ “ጓዟ”፥ “ግዛቷ” እና “የሀብት፥ የገንዘብ ማከማቻ ግምጃ ቤቷ” ከሚለውም ትርጓሜ ጋር አያይዞ ማጤኑ ተገቢ ይኾናል፡፡ ለዚህ እውነታ ማጠናከሪያ፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን፡ በኢየሩሳሌም ያላቸውን ዐፅመ ርስት፡ እስካኹን ሳይለቀቁ መኖራቸው፡ ለዚህ ማስረጃነት ይበቃል፡፡ ይህን ሓተታ በሚመለከት፡ በበለጠ ለመረዳት፡ ***“ኢትዮጵያዊው፥ በማንነቱ ፍለጋ!”*** ፥ ***“ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!”*** ፥ **Ethiopia: The Classic Case** እና በሦስት ጥራዞች የተከፋፈለውን፡ **“ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት”**፡ የሚሉትን መጻሕፍቴን ማንበብ ይቻላል፡፡

እንግዴህ፡ ኢየሩሳሌምና ጋዛ፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ እንዲህ ያለ፡ ዓለም ያወቀውና ፀሓይ የሞቀው አግባብነት ያላቸው መኾኑ፡ በገሃድ የታመነበት ሲኾን፡ ይህ እውነታ፡ ዛሬ፡ በዚሁ የጋዛ ሓተታ ውስጥ፡ እንዴት ሳይጠቀስ ሊዘነጋና ሊታለፍ ቻለ? እንዲህ የኾነበትን ምክንያት፡ ለመገመትም እንኳ ያዳግታል! ያውም፡ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ተብሎ በተቋቋመው፡ በዚህ አገልግሎታችሁ? ያውም፡ በኢትዮጵያዊነታችሁ ጸንታችሁ ለመገኘታችሁ በማትጠረጠሩት በእናንተ ዘንድ?

ስለምትሰጡኝ መልስ፥ ምናልባትም፡ ጥያቄዬና መልሳችሁ፡ ለአድማጮች እንዲሰማ የምታደርጉ ከኾነ፡ ለዚሁ ጠቃሚ ምግባራችሁ ጭምር፡ አስቀድሜ “እግዚአብሔር ይስጥልኝ!” እላለሁ፡፡

ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደኢየሱስ
የአገልግሎቱ ተጠሪ